# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!






- ⇒ የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?
- ⇒ ማገልገል ይፈልጋሉ?
- ⇒ Yeec.org App ጭነዋል?
- ⇒ http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?

**ሽማግሌዎችን ለማግኘት፡-**

**773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)**
**773-507-0147 (ወ/ም ጸደቀ)**
**630-677-0293 (ዶ/ር ተረፈ)**
**773-910-0486 (እ/ት ሰናይት)**
**773-556-5345 (ወ/ም ረድኤቱ)**

**<u>መደበኛ ፕሮግራሞች</u>**

እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.
አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m.

---

| የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን | | Chicago Yemsrach Evangelical Church |
|---|---|---|

“እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ” ሉቃስ 2፡10



“This book of the law shall not depart from your mouth, but you shall meditate in it day and night, that you may observe to do according to all that is written in it. For then you will make your way prosperous, and then you will have good success.”

Joshua 1:8

“የዚህ ሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ ነገር ግን የተፃፈበትን ሁሉ ትጠብቅና ታደርግ ዘንድ በቀንም በሌሊትም አስበው የዚያን ጊዜ መንገድህ ይቃናልሃል ይከናወንልሃልም” (ኢያሱ 1፡8)

Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625

**መደበኛ ፕሮግራሞች**
እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.
አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m.

**August 04, 2019** | **ሐምሌ 28 ፣ 2011 ዓ.ም.**

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| ጸሎት ............................ | ወንድም ረድኤቱ ካሳ |
| አምልኮ.......................... | የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ቡድን |
| ፕሮግራም መሪ ............. | ወንድም ሲሳይ መሸሻ |
| ቃል ................................ | ወንድም ፍቅሩ ካዮ |
| ማጠቃለያ ..................... | ፕሮግራም መሪ |

### የሳምንቱ ጥቅስ

**“ የልመናዬን ድምጽ ሰምቶአልና፡**
**እግዚአብሔርን ወደድኩት።**
**ጆሮውን ወደ እኔ አዘንብሎአልና፡**
**በሕይወት ዘመኔ ሁሉ ወደ እርሱ እጣራለሁ።**
(መዝሙር. 116፡1-2)

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች**

| መሪ | ቀን | አድራሻ |
|---|---|---|
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7319 N Oakley Ave, Chicago, IL 60645 |
| ወ/ም ጌቱ ጳውሎስ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሃሙስ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| | | |

## መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድዔቱ ካሳ

### የኤልሳዕ አጥንት!

*ከጥቂት አመታት በፊት በሃገራችን በጣም የታወቀ ስመጥሩ አገልጋይ ጌታን እንዴት እንደተቀበለ ሲናገር በስደት ከሃገር ለመውጣት ጅቡቲ እያለሁ ወችማን ኒ (Watchman Nee) የተባለው የእግዚአብሔር ሰው የጻፈውን መጽሐፍ አነበብኩ ፤ ያ መጽሐፍ ለኔ እንደ ኤልሳዕ እጥንት ሆኖ በድኔን አስነሳው አለ። እንደምታስታውሱት ነብዩ ኤልሳዕ ከሞተ በኋላ መቃብሩ አጠገብ ሰዎች እንድ የሞተ ሰው ሊቀብሩ ሲሉ ለ ደጋ ጣዮችን አይተው በመፍራት ሬሳውን በኤልሳዕ መቃብር ላይ ጣሉት። ያ በድን የኤልሳዕን አጥንት ሲነካ የሞተው ሰው ድኖ በእግሩ ቆመ። (2 ነግ 13፡21 ) ይህ የአገራችን እውቅ አገልጋይ የወችማን ኒን መጽሐፍ ከኤልሳዕ አጥንት ጋር ነው ያነፃፀረው። የኤልሳዕ አጥንት በድን እንዳስነሳ እንዲሁ ፡ የወችማን ኒ መጽሐፍ በወቅቱ በመንፈስ ሙት ለነበረው ሰው የእግዚአብሔርን እውነት በመግለጽ ከሞት ወደ ሕይወት እንዲሸጋገር ረዳው። በኤልሳዕ አጥንት ውስጥ አልፎ የእግዚአብሔር መንፈስ የሞተን ሰው ሕያው እንዳደረገ ሁሉ እንዲሁ በተፃፈው ወችማን ኒ መጽሐፍ ገፆች ውስጥ የእግዚአብሔር መንፈስ አልፎ ለዚህ ሰው ሕይወትን ሰጠው። በእርግጥም የወችማን ኒ መጽሐፍቶችን ያነበባችሁ ወይንም የምታነቡ ይህ እያልኩት ያለሁት ነገር ምን እንደሆነ ይገባችኋል። የእግዚአብሔር ሰው ወችማን ኒ የጻፏቸው መጽሐፎች ጥልቅ መንፈሳዊ እውነቶችን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ስለሚያስተላልፉ የሰዎችን ሕይወት ይነካሉ።*

ወችማን ኒ አስደናቂ ሕይወት ያላቸው ክርስቲያን ነበሩ። በትውልዳቸው ቻይናዊ ሲሆኑ ጌታን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው የተቀበሉት በ17 ዓመታቸው ነበር። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ህይወታቸውን ለጌታ አገልግሎት ሰጥተው ኖረዋል። በቻይና ኮሚኒስቶች አለቅጥ ተሰቃይተዋል። የእድሜያቸውን የመጨረሻ 20 ዓመታት ያሳለፉት በእስር ነበር። ወችማን ኒ የስነ-መለኮት ትምህርት ቤት ገብተው አልተማሩም ነገር ግን አስደናቂ የክርስትና መርህ መጽሐፍትን አበርክተዋል። ሃምሳ የሚሆኑት መጽሐፍቶቻቸው ወደ እንግሊዘኛ ተተርጉመዋል። መጽሐፍ ቅዱስን በጥልቀት በግላቸው ከማጥናት በተጨማሪ 3000 በላይ የሚሆኑ መጽሐፍትን ያነበቡ ሲሆኑ ፡ የገቢውንም አንድ ሶስተኛ የሚያጠፉት በመጽሐፍት ላይ ነበር። (ሌላውን እንድ ሶስተኛ ሌሎችን ለመርዳት ሲጠቀሙ የሚኖሩት በቀሪው አንድ ሶስተኛ ነበር)።

የወችማን ኒን ታሪክ ያነሳነው የመጽሐፍትን ጉልበት ለማሳየት ነው። የኛ ሕዝብ የማንበብ ባህል የለውም ይባላል። ይህ መቼም ትልቅ ጉድለት ነው። ማንበብ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። ብዙ ነገር የምናውቀው በትምህርት ቤት አይደለም ይልቁንም በማንበብ ነው። በተለይም እንደ ክርስቲያን የማንበብ ባህል ሊኖረን ይገባል። ቅዱሳን ሰዎች የሚጽፉት መጽሐፍት የእግዚአብሔር መንፈስ ይተላለፍበታል። እንዲሁም ደግሞ አንድ መጽሐፍ ማለት የአንድ ሰው የሕይወት ዘመን ልምድና ማስተዋል የታጨቀበት ነው። መጽሐፍትን በማንበብ ልምዶችን ማግኘት ፡ ሌሎች ባህሎችን ለመረዳት እንችላለን። እንደ ክርስቲያን የአምላካችንን ፍቃድ ፡ ሃሳብ ፡ ትእዛዝ ወዘተ የምናውቀው ቅዱስ ቃሉን በማንበብ ነውና በርትተን ማንበብን እራሳችንን እናስለምድ።

ጌታ ይርዳን እላለሁ። አሜን!